የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፰<br>አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺ ዓ.ም | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 14th Year No 38<br>ADDIS ABABA 27th May, 2008 |

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፪/፪ሺ ዓ.ም

ለሳውላ ቀይ አፈር የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዓቀፍ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ...... ገጽ ፬ሺ፩፻፰

**Proclamation No. 582/2008**

OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Sawla Key Afer Rural Electrification Project Ratification Proclamation Page 4108

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፪/፪ሺ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዓቀፍ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሳውላ ቀይ አፈር የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፳ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /ሃያ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዓቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፱ ቀን ፪ሺ፯ በቪየና የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፴ ቀን ፪ሺ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «ለሳውላ ቀይ አፈር የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዓቀፍ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፪/፪ሺ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 582/2008.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

**WHEREAS**, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development stipulating that the OPEC Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in the amount of 20,000,000 US Dollars (Twenty million US Dollars) for financing Sawla Key Afer rural electrification project was signed in Vienna on the 19th day of November, 2007;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Financing Agreement at its session held on the 8th day of May, 2008;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Sawla Key Afer Rural Electrification Project Ratification Proclamation No. 582/2008".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዓቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፱ ቀን ፪ሺ፯ በቪየና የተፈረመው ቁጥር 1153P የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /ሃያ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Loan Agreement Loan Number 1153P signed in Vienna on the 19th day of November 2007 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 20,000,000 US Dollars (Twenty million US Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of May, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**